# ጠበል



"ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ለውሶ  የዕውሩን ዓይኖች ከቀባ በኋላ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ዓይንህም ይበራል"/ ዮሐ ወንጌል 9፥6-8/።

ጠበል ማለት ቃሉ የግእዝ ሲሆን ፍቹም  አፈር (አቧራ) ማለት ነው። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናችን ጠበል ብለን የምንጠራው በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ማለት ነው።

ጠበል ማለት በግእዙ አፈር (አቧራ) ማለት ከሆነ ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ለምን ጠበል ተባለ? የሚል ጥያቄ ቢኖር መልሱ በዮሐንስ ወንጌል 9፥6-8 የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉም እንዲህ ይላል "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ። ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ፤ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው። ስለዚህም ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ" ይላል። በዚህም ምንባብ ውስጥ እንደምንመለከተው አንድ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ብርሃን ዕውራን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ተዋሐደ አምላክ ነውና አፈሩን በምራቁ ለውሶ የዕውሩን ዓይን ከቀባ በኋላ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ዓይንህም ይበራል ስላለው የተባለውን ፈጽሞ ዓይኑ በርቶለታል።ይህ ተአምር የተደረገው ሥጋን የተዋሐደ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ለውሶ ጭቃ ባደረገው መሬትና በሰሊሆም መጠመቂያ ከሚገኘው ቅዱስ ውኃ ድብልቅ በመሆኑ ሕሙማን የሚፈወሱበት ቅዱስ ውኃ ጠበል ተብሎ ተጠርቷል።

## ስለጠበል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች

1ኛ) ንእማን የተባለ ከፍተኛ የሶርያ ባለሥልጣን ነበር። ይህም ሰው ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ እንደበረዶ ነጭ በሆነ ለምፅ የነደደ ነበረ። ከአገሯ ከእስራኤል ወደ ሶርያ ተማርካ የሄደችና በዚህ በለምፅ በሽታ በተያዘው ባለሥልጣን ቤት የነበረች አንዲት እስራኤላዊት ብላቴና በእስራኤል ምድር ለምፅን የሚፈውሱ

ነቢያት አሉ። ንእማን ቢሄድ ይድናል ብላ በተናገረችው መሠረት ለምፃሙ ምእማን ሠራዊት አስከትሎ ወደ እስራኤል በመሄድ ከነቢዩ ከኤልሳዕ ጋር ተገናኝቶ ስለበሽታው ሲወያዩ ነቢዩ ኤልሳዕ ለንእማን ከለምፅህ የምትነፃው በዮርዳኖስ ውኃ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለህ ታጥበህ ስትወጣ ነው አለው። ንእማንም ሰው በውኃ ከበሽታ እንዴት ይድናል? ብሎ በአሁኑ ዘመን እንደሚጠራጠሩት እንደ እንዳንድ ሰዎች የውኃ ውኃማ በአገሬ በደማስቆ የሚገኙት ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእስራኤል ወንዞች አይሻሉምን? በማለት በከፍተኛ ብስጭት ወደ አገሩ ሲመለስ የራሱ ተከታዮች የከበደ ነገር አልጠየቀህም አምነህ በውኃ ታጠብ ነው ያለህ ለምን አትታጠብም አሉት። የተከታዮቹንም ቃል በመስማት ተመልሶ በእምነት በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ ሲወጣ ከለምፁ ተፈውሷል። /2ኛ ነገሥ. 5÷1-15/። በተለይም ቁጥር አስራ አራትን ይመልከቱ።

2ኛ) በኢየሩሳሌም ውስጥ ቤተ ሰይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ እንደነበረችና በእርሷም ውስጥ ያለውን ውኃ የ እግዚአብሔር መልአክ እየባረከው በዚህ ቅዱስ ውኃ በሽተኞች፣ እውሮች፣ አንካሶች፣ ሰውነታቸውም የሰለለ ሁሉ ይድኑ እንደነበረ እንረዳለን። ዮሐ.5÷ 2-5። በዚህ በተጠቀሰው ምዕራፍና ቁጥር ውስጥ 38 ዓመት ሙሉ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዞ የኖረ አንድ በሽተኛ ሰው እንደነበረና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ሰው በዚያው ቦታ አግኝቶት ልትድን ትወዳለህን? ብሎ በጠየቀው ጊዜ መልአኩ ውኃውን ሲባርከው ውኃውም ሲንቀሳቀስ ወደ ውኃው የሚያስገባኝ ዘመድ በማጣቴ እንጂ እኔማ እድን ዘንድ እወድ ነበር ብሎ ስለመለሰለት እንደ ኤልሳዕ በውኃ ታጠብ ሳይል በቃሉ ብቻ ተነሳ አልጋህምን ተሸክመህ ሂድ በማለት ፈውሶታል።

ይህንን መንሥኤ በማድረግ በአዲስ ኪዳን በቃሉ ብቻ እንጂ ጠበል የተባለ ውኃ አያስፈልግም የሚሉ አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጠበሉ የሚያስገባው ዘመድ ያጣውን ይህንን ሰው ወደ ውኃ በማስገባትና በውኃው በመፈወስ ፈንታ በቃሉ ብቻ የፈወሰው በአዲስ ኪዳን ጠበል የተባለ ቅዱስ ውኃ አያስፈልግም ለማለት አይደለም። እኛ የሰው ልጆች በምንታመምበት ጊዜ ወደ ጠበል የሚወስደን ዘመድ ብናጣ ባለንበት አልጋ ላይ ሆነን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ማረን ብለን ብንጸልይ ምልዓተ መለኮቱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ አምላክ በቃሉ ብቻ የሚፈውሰን መሆኑን ሊያረጋግጥልን ስለፈለገ ብቻ ነው። ይልቁንም የጠበሉ ባለቤት አምላካችን ራሱ በዚያ በመገኘቱና ለዚህ ሰው ወደጠበሉ መሄድ ስላላስደለገው ነው።

3ኛ) በሐዲስ ኪዳን ጠበልን ባርኮ እንደሰጠን ተጨማሪ መረጃ “ሲያልፍም (አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ። ደቀ መዛሙርቱም መምህር ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ ብለው ጠየቁት። ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ። የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሰሩም። ብርሃን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልባት

ሌሊት ትመጣለች። በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ፤ በምራቁም ጭቃ አድርጐ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ስለዚህ ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ" /ይላል ዮሐ 9፥1-8/። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሁሉን ቻይ አምላክ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ይህን ዓይን የሌለውን ዕውር በሰሊሆም መጠመቂያ ታጥበህ ዓይንህ ያበራል ብሎትና ሰውየው እንደታዘዘው ተጠምቆ ዓይኑ የበራለት በቃሉ ብቻ ዓይኑን ማብራት አቅቶት ሳይሆን በብሉይ ኪዳን ሕሙማን ይፈወሱበት ተአምራት ይደረግበት የነበረው ቅዱስ ውኃ (ጠበል) በሐዲስ ኪዳንም የተባረከና ፈቅዶ የሰጠን ጸጋ መሆኑን ለማስረዳት ነው።

ይህ መረጃ የሚቀርብበት ጊዜ መልካም መቀበሉንስ እንቀበለው ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ. 14፥14 ሁሉን ነገር በስሜ ለምኑ ይልና በተጨማሪም በሐዋ. ሥራ 4፥12 ላይ "ከሰማይ በታች ከምድር በላይ መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድነበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ሌላ የለም" ይላል። ስለዚህ ጠበሎች ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠራት ሲኖርባቸውና አዳኙም እርሱ መሆን ሲገባው ለምን የድንግል ማርያም ጠበል፣ የሚካኤል፣ የገብርኤል፣ የጊዮርጊስ፣ የገብረ መንፈስ ቅዱስ ወዘተ...ጠበል ተባለ? የሚሉ አሉ።

መልሱ አጭር ነው። ይኸውም በጠበሉ ቅዱሳኑ እንዲታሰቡበት ነው። በኢሳይያስ 56፥4-6 ባለው ምንባብ ውስጥ፥ "ደስ የሚያሰኘኝን ነገር ለመረጡ ቃል ኪዳኔንም ለጠበቁ ጃንደረቦች ከሴቶች ልጆችና ከወንዶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ በቤቴና በቅጥሬ መታሰቢያቸውን አደርጋለሁ። የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣችዋለሁ" ባለው ቃል መሠረት ነው። እዚህ ላይ ጃንደረባ የሚለው ቃል በማቴዎስ 19፥12 ላይ ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉ አሉ። በማለት የዚህን ዓለም ፍትወቱን፣ ፍቅሩን ሁሉ ትተው መስቀሉን ተሸክመው በብቸኝነት ራሳቸውን ያሳለፉትን ቅዱሳኑን መሆኑን ያረጋግጣል።በተጨማሪም "የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ነው" ይላል /ምሳሌ. 10፥7/። በዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መሠረት በጠበሉ ቅዱሳኑ መጠራታቸው መታሰቢያቸው እንዲሆን ነው። መታሰቢያነት ብቻም ሳይሆን በረከትነትም አለው ብለን እናምናለን እንጂ ጠበሉን የፈጠረው መድኃኔ ዓለም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑና በጠበሉም አድሮ ሕሙማንን የሚፈውሰውና ተአምራትንም የሚደረገው ሁሉን ቻይ የሆነው የአምላካችን የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑ ጠፍቶን አይደለም። በጠበል ታጥበን እንድንፈውስ የሆነው በሚታዩ በሚጨበጡ ቅዱሳት ምልክቶች የማይታየውን የማይጨበጠውን አጋንንትን ማባረር፣ ሕሙማንን የመፈወስ ተአምራትን የማድረግ ረቂቅ ኃይሉን እንዲያስተላልፍባቸው ስለፈቀደ ነው። ለምሳሌ ያህል ፦

1. የኤርትራ ባሕር የመክፈል ኃይሉን በሙሴ በትር /ዘጻ. 14፥15-17/።
2. ሙት የማስነሳት ኃይሉን በዐፅመ ኤልሳዕ /2ነገ 13፥20/።
3. ደዌያትን የመፈወስ ኃይሉን በቅዱስ ዘይት /ማር. 6፥14 ፤ ያዕ 5፥14/።
4. አጋንንትን የማባረር ኃይሉን ቅዱስ ጳውሎስ ለብሶት በነበረው ልብስ /የሐዋ. ሥራ 19-11/።

እንዳስተላለፈ ሁሉ በዚህ ጠበል ተብሎ በተጠራው በቅዱሱ ውኃም እስከ አሁን ድረስ ወደ ፊትም ሕሙማንን የመፈወስ ተአምራትን የማድረግ ረቂቅ ኃይሉን እያስተላለፈልን እየተፈወስን እንገኛለን። ለዚህ ምሳሌ የአዲስ አበባ ኪዳነ ምሕረትን፣ ተክለ ሃይማኖትን፣ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ዑራኤልን፣ የሚጣቅ አማኑኤልን፣ የለብቃ ኢየሱስን ጠበል መጥቀስ በቂ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ኃይሉን በገለጠባቸው ማደሪያዎቹ ባደረጋቸው የጠበል ቦታዎች ሰዎች ከደዌ ሥጋ ተፈውሰው ከሥቃይ አምልጠው በሰው ፊት እንደ ሰው ለመኖር በቅተዋል። ንእማን የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ኤልሳዕ የነገረውን ሰምቶ በሃይማኖት ወደ ዮርዳኖስ ወረደ፣ ተጠመቀም፣ በሰዎች ፊት ያሳፍረው የነበረው ሰዎች ከሚያዩት ለምፅ ነፃ ተፈወሰ፤ ቡራቡሬ የነበረው ሰውነቱ እንደሕጻን ልጅ ገላ ታደሰ፤ አዲስ ሰው ሆነ።

እንዲሁም ዛሬም የቤተ ክርስቲያንን አባቶችና አባታዊ ምክራቸውን፤ ትምህርታቸውን ሰምቶ እግዚአብሔር በሚያደርገው ድንቅ ተአምር ሳያንጐራጉሩ ማመን፣ ሳይጠራጠሩም እግዚአብሔር የኃይሉ መግለጫ ባደገረው ቅዱስ ጠበል በመጠመቅ አፍአዊ ከሆነ በሽታ መፈወስ ብቻ ሳይሆን መምህራን የሚነግሩንን አማናዊ ቃለ ሕይወት ሰምቶ ውስጣዊ ከሆነና እግዚአብሔር ብቻ ከሚያየው የኃጢአት ለምፅና በሽታ መዳን ያስፈልጋል። ትውልዱ የእግዚአብሔርን ሥራ ማመን ሲቸግረው ለእግዚአብሔር የሚሆን ልቡና፤ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚገልጽበት የተቀደሰ ሕይወት ሲያጣ እግዚአብሔር ኃይል የሚያደርግባቸውን የድኅነት ምክንያቶች ሁሉ እየካደ ባለበት ዘመን የምንገኝና ክርስቲያን ነን የምንል የዘመኑ ሰዎችም ከዚህ ርቀን  ይልቁንም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፤ ማደሪያዎቹ መሆናችንን አምነን እግዚአብሔር በሕይወታችን፣ በንግግራችን እንዲያድር የኃጢአት ለምፅ፣ የቅናትና የክፋት ለምፅ የሚያሰቃያቸውን ወገኖች በማዳን ምክንያት ለመሆን እንዘጋጅ።

ይህ ብቻ አይደለም እንግዲህ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ የእኛስ ሰውነት የቱን ያህል ተለውጦ ለሰዎች ሕይወት መዳን አብነት ሆኖ ይሆን? የንእማንን በመሰለ አፍአዊ ለምፅ፣ የመፃጉዕን በመሰለ ሽባነት በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ዘጠኝ እንደተጠቀሰው ባለ የዓይን ዕውርነት ሳይሆን ውስጣዊ ለምፅ የያዛቸውንና ሕይወታቸው ቡራቡሬ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የሚያሳርፋቸው በኃጢአት በሽታ ሽባ ሆነው ወደ መዳኛይቱ አማናዊት ቤተ ሳይዳ (ቤተ ክርስቲያን) የሚወስዳቸው አጥተው ለዘመናት በዚህ ደዌ ኃጢአት የሚሰቃዩትን፤ በሥጋቸው የሚያዩ እየመሰላቸው በአእምሮአቸው የታወሩትን፤ በነፍሳቸው በጨለማ ሕይወት የሚመላለሱትን ዕውራነ ልቡና በእግዚአብሔር ቃል የሚያነፃ፤ የሚፈውስና የሚያበራ ሕይወት ያለው ክርስቲያን ነው፤ በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው፤ እውነተኛ ክርስቲያን ሊባል የሚችለው።

የብዙዎች ሕይወት (ኑሮ) ሥራችንና ንግግራችን ሰዎችን የኃጢአት ለምፅ የሚያስይዝ፣ ጤነኛውን በሽተኛ የሚያደርግ፣ ደዌ ነፍስ የሚያስይዝ፣ ልቡናው ብሩህ የሆነውን የሚያሳውርና ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚመልስ ለሕይወት ለሚጠራ ይልቅ

ከቤተ ክርስቲያን የሚያርቅ፣ ከሕይወት የሚያሸሽ በሆነና በመመላለስ ብቻ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከዮርዳኖሱ ውኃ ከቤተ ሳይዳውና ከሰሊሆም መጠመቂያ እጅግ አንሰን እንታያን። እግዚአብሔር አክብሮ ማደሪያዎቹ አድርጐናልና ማንነታችንን ረስተን የእኛ በምንለው የአላዋቂዎች ጥበብ ከእግዚአብሔር የማዳን ኃይል እንዳንርቅ ከቸርነቱም እንዳንወጣ በሥራው ላይ ከማመጽ ይልቅ በንስሐ ራሳችንን ብናርም፣ ሕይወታችንን ብንለውጥ፣ ልቡናችንን ብናድስ መልካም መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል።/ሮሜ 12÷2/። ስለዚህ ካስነወረን የኃጢአት ለምፅ፤ ሽባ ካደረገን ከኃጢአት ደዌ፣ ምስጢርን ሰውሮ፣ ማስተዋልን አጥፍቶብን፣ በልቡናችን ዕውር ካደረገብን የትዕቢት በሽታ የሚያነፃውን የንስሐ ሕይወት ገንዘብ አድርገን በማየ ገቦው ታጥበን በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ታትመን ዘላቂ ለሆነ ሕይወት መንግሥት ሰማያት እንድንበቃ እግዚአብሔር በቸርነቱ፣ ወላዲተ እምላክ በረድኤቷ፣ መላእክት በጥበቃ፣ ቅዱሳን በአማላጅነታቸው ከሁላችን ጋር ይሁኑ።

ወይትባረክ እግዚአብሔር

አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ
ከሐመር የካቲት 1985 ከጻፉት ላይ የተወሰደ